# ልጅነት በ“ዘላን” እና “አለንጋና ምስር”፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ

ቴዎድሮስ አለበል[1]

***አኅጽሮተ ጽሑፍ፡-*** *ይህ ጥናት የአዳም ረታ ስራ ከሆነው “አለንጋና ምስር” የአጫጭር እና ኖቬላ ልቦለዶች መድበል ውስጥ በተመረጡ ሁለት ቴክስቶች (“ዘላን” እና “አለንጋና ምስር”) ላይ የሥነ ልቡና ንድፈ ሃሳቦችን ምቹ በሆነ ስልት በማልመድ የተደረገ ነው፡፡ በቴክስቶቹ ውስጥ የተቀረጹ ልጅ ገፀ ባህሪያትን ከማኅበረ-ልቡናዊና ‹‹ሳይኮሴክሿል›› ማንነት፣ ‹‹ኤዲፐሳዊ ቅዠት›› (Oedipus complex) እና ‹‹ፍቅዓተ-ኢጎ›› (splitting of the ego)፣ የጨቅላነት ‹‹ግንትሮሽ›› (fixation) እና የሁለት ሰብዕናዎች መቃየጥ አንጻር ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ሚቶሎጂዎች የተቀዱ መባያዎች ሰብዕናን መርምሮ ለማሳየት ትኩረት ተደርጎባቸዋል፡፡ ጥናቱ ወዲህ በቴክስቶቹ ውስጥ የተቀረጹ ልጅ ገፀ ባህሪያት የብቸኝነት፣ የመከዳትና የመጣል ስሜት የሚስተዋልባቸው እንደሆኑ፣ ወዲህ ደግሞ የአሳዳጊዎቻቸው ሚና አፍራሽ መሆኑ፣ የጨቅላነት ‹‹ሳይኮሴክሿል›› ዕድገት የ‹‹ግንትሮሽ››ና የ‹‹ሣቃዪ ፍለሳ›› (sadistic displacement) ማደሪያዎች እንደሆኑ ተብራርቷል፡፡ ስለሆነም፣ በእነዚህና በትንተናው ውስጥ በ“ተዘነቁ” ሃሳቦች ልጆቹ ማኅበረ-ባህላዊ ኃላፊነትን መሸከም የማይችሉ እንደሆኑ ለማጠቃለል ተሞክሯል፡፡ በመጨረሻም በቴክስቶቹ ውስጥ ልጆቹ የተቀረጹት፣ ማኅበረ-ባህላዊ ስርዓቶችና ተፈጥሯዊ ማንነቶች በመጎራበት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡*

**ቁልፍ ቃላት**፡- *ሣቃዪ ፍለሳ፣ ራስ ድሪያ፣ ሳይኮሴክሿል፣ ግንትሮሽ፣ ኤዲፐሳዊ ቅዠት፣ ፍቅዓተ-ኢጎ*

## *መግቢያ*

ሥነ ጽሑፍ እንደሙያ መታየት ከጀመረበት ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ የአጠናን ስልቶች ተቀምረዋል፡፡ የከያኒውን ስሜት አጥብቀው ከሚፈልጉት *Romanticism* መራሹ ሒስ እስከ “አፍቃሬ-አንባቢ”ው *Reader-response*፣ በራቸውን ከዘጉ (ቴክስታዊ[2] ንባብን ብቻ

[1] **ቴዎድሮስ አለበል** በመደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ፣ በቋንቋዎች ጥናት ትምህርት ቤት፣ በአማርኛ ቋንቋ እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ሌክቸረር ነው፡፡ Email: tediyo417@gmail.com

[2] ***ቴክስት*** እያልኩ የምጠቀመው በቀጥታ የእንግሊዘኛውን ነው፡፡ በዘመነኛው የፍከራ ሒደት ***ቴክስት*** የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ማንኛውንም ፍች ሊፈለቀቅበት የሚችልን ነገር ሁሉ ይመለከታል፡፡ ስዕል፣ ሙዚቃ፣ ቅርጻ ቅርጽ፣ ሥነ ጽሑፍ … ቴክስት ናቸው፤ አንዳች ፍች የሚፈልቅባቸው (Cavallaro፣ 2001)፡፡ ከምንባብም የሚዘልና ጥቅል ጽንሰ ሃሳብ ነውና በአማርኛ አቻ ፍች ለማግኘት አልተቻለኝም፡፡ ስለሆነም በዚች ሒሳዊ መጣጥፌ ውስጥ፣ እስከዛው ድረስ፣ ቃሉን በቀጥታ እጠቀመዋለሁ፡፡

ንባብ ለማኼድ ያገለገሉ ንድፈ-ሃሳቦች ከሥነ ልቡና ቤት የለመዱ ናቸው፡፡ የኤሪክሰን ማኅበረ-ልቡናዊ ዕድገት (psychosocial development of human being) (ኤሪክሰን፣ 1959፣ ገጽ 55-99፤ 1963፣ ገጽ 222-242)፣ ፍሮይዳዊው "ፍካሬ-ልቡናዊ የሰብዕና ቅጥ" (psychoanalytic model of personality)ና "ሳይኮሴክሿል" (ፍሮይድ፣ 1905፣ ገጽ 173-199፤ እነ ጉሪን፣ 2005፣ ገጽ 156-161) የዕድገት ደረጃዎች እንዲሁም እነዚህ ንድፈ-ሃሳቦች በራሳቸው የሚጠሯቸው ላካናዊ የፍካሬ-ልቡና ጽንሰ-ሃሳቦች ተመልክተዋል፡፡ ቴክስቶቹ ዓላማዊ የናሙና (purposive sampling) ዘዴን በመጠቀም የተመረጡ ናቸው፡፡ አጥኚው የ"ልጅነት" ሥነ-ልቡናዊ እሳቤዎች የገዘፉባቸው እንደሆኑ አጥብቆ ያምናልና ነው፡፡

## "ልጅነት"፤ ማኅበረ-ባህላዊ ፍንገጣና የሣቃዪ ፍለሳ[5] ማደሪያ

> Thus sadism would correspond to an aggressive component of
> the sexual instinct which has become independent and exaggerated
> and, by displacement, has usurped the leading position.
> (Freud, 1905, p.158)

የፍሮይድን ሃሳብ ወደ አማርኛ ብናለምደው፣ "በሌሎች የስሜት መጨቆን መደሰት (sadism) ጤናማ ያልሆነ ፍትወታዊ ደመ ነፍስ ሲሆን ቦታውን በሌላ ተመሳሳይ አካል በመተካት የሚገኝ የ"ጓነ" እርካታ ነው" የሚል ይሆናል፡፡ በዚህ ሃሳብ ወደ ልቦለዷ ታሪክ መዝለቅ ይቻላል፡፡ የልቦለዷ የታሪክ ባለቤት ተሻለ አደፍርስ ነው፡፡ እናቱ ስሙን ያወጣችለት በፍቅር የምትንገበገብለት አባቱ፣ አደፍርስ፣ ፍትወታዊ ፍላጎቱን ካደረሰ በኋላ ጥሏት በመሰወሩ ከአባትህ ብትሻል ብላ ነበር፡፡ ተሻለ በዚህ ልቡናዊ ቀውስ ውስጥ ባለች እናቱ በማደጉ የእናቱ  በሰዎች ስሜት መደሰት (sadistic displacement) የአጸፋ ስልት ታላሚ ነው፡፡ የእናቱ  አደፍርስን የመበቀል ኢ-ንቁ ልቡናዊ ግፊት የሚያርፈው በእሱ ላይ ነው፡፡

"የት አደርክ?"
ዝም፡፡

---

[5] ይህን ጥምር ቃል ለ"sadistic displacement" አቻ አድርጌ ተገልግየበታለሁ፡፡ "sadism" በሌሎች ሰዎች ላይ በሚደረግ ጭካኔ የሚገኝ ደስታ ነው (Ribas፣2005፣1525)፡፡ "Displacement" አንድ ሰው ወይም ሁነት በሌላ ሰው ወይም ሁነት የሚወከልበት ትዕምርታዊ መተካት ነው (እነ Krishnaswamy፣2004፣ ገጽ 50)፡፡ ስለሆነም ጥምር- ቃሉን መጠቀም፣ "እስከ ጊዜው ድረስ"፣ ክፋት የለውም፡፡ "ለምን ቢሉ?" ኪዳነ ወልድ ክፍሌ "***ሣቃዪ***፤ የሚሣቅይ፤ መከራ፡የሚያሳይ፤ አስጨናቂ (ኪዳነ ወልድ፣ 1948፣ ገጽ 674)፡፡ ***ፍልሰት***፤ መፍለስ፤መፍረስ፤መሰደድ፤ተማርኮ፡መኼድ፤መዞር፡ መባከን፤ወደ ሌላ ሕዝብ መጠጋት… መለየት… ***አፍለሰ***፤ አፈለሰ፤አስፈለሰ፤ነቀለ፡አስነቀለ፤ማረከ፡አስማረከ፤ አሳደደ፤ አራቀ፤ካገር አሶጣ፡አስለቀቀ…ለወጠ፤ገለበጠ" በማለት ቃላቱን ያፍታታሉና (ኪዳነ ወልድ፣ 1948፣ ገጽ 725)፡፡

እግር “ፌቲሻዊ”[10] አካል ነው፡፡ “ይሮጣል” የሚለው የለዋጭ ዘይቤን[11] ሚና ይዞ የገባ ቃል ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ከብዙ ሴቶች ጋር ፍትወት የሚፈፅም አባሉን “ተጓዥ ነው!”፣ “ይሄዳል!” ወዘተ. በሚሉ አባባሎች ሲገልፅ መስማት የተለመደ ነው፡፡ አንድም ይሄን ቃል በበለጠ “አጽኖ” ለማቅረብ ጥቅም ላይ የዋለ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድም ፍትወታዊነትን የሚገልፀውን ቃል የአገባብም ሆነ የፍች ሚና ነጥቆ የመጣና “ዋናውን” (original) ቃል ወደ “ተወካይነት” ያወረደ ሊሆን ይችላል፡፡ ንቁ ልቡና ከኢ-ንቁ ልቡና ጋር ያለውን “መሰናሰል” የገለጠም ነው፡፡ ይህን የፍች ሚናና ተሰናስሎ ይዘን ስንጓዝ የበላይን በግብር “ዘማዊነት” ያስረግጥልናል፡፡

ሌላው በተጓዳኝነት የሚነሳው የጨቅላነትና የወጣትነት ንቁና ኢ-ንቁ ልቡናዊ ርስትን የመጠበቅ ፍላጎት “መቃየጥ” ነው፡፡ ዝቅ ብለን እንደምንመለከተው፣ ተሻለ ወደ “ሥርዓተ ትእምርት” (symbolic order) ከመሸጋገሩ በፊት በእናቱና በእሱ መካከል ልዩነት እንዳለ አይረዳም፤ እንደመጀመሪያ የፍትወት ማደሪያውም አድርጎ ይወስዳታል፡፡ ወደ “ሥርዓተ ትእምርት” ደረጃ ሲሸጋገር ግን ትክክል እንዳልነበረ ይረዳል፡፡ ማኅበረ-ባህላዊ፣ መንፈሳዊና ግብረ-ገባዊ እሴቶች ከዘመድ ጋር የሚኖር ፍትወታዊ ፍላጎትን ‹‹ሕሩም›› (taboo) እንደሆነ ያሳውቁታል፡፡ እናቱ የአባቱ “ርስት” እንደሆነችም ይገነዘባል፡፡ ይችን “ርስት” ከሌላ ወንድ ሲጠብቅ፣ በፈጠረችውም ግንኙነት ጥላቻን ሲሰንቅ እናስተውላለን፡፡ በተለይም ዳይሬክተሩን የሚጠላቸው የርስት ድንበሩን ስላፈረሱበት ነው፡፡ የሚከተለው አስረጅ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡

*ማስታወቂያ*

1. *የዳይሬክተሩ መላጣ ያስጠላል፡፡ የብርቱካን ውሽማ ናቸው፡፡*
2. *ቲቸር በላይ ሰካራም ናቸው፡፡ የኮታቸው ኪስ ተቀድዷል፡፡*

---

[10] ፍሮይድ ***Fetishism***ን የመጀመሪያዋን የፍትወት ማደሪያ (Sexual object)፣ እናት፣ ምቹ ባልሆነ የእርካታ ማግኛ መተካት እንደሆነ ያስረዳል፡፡ እግር፣ ፀጉር፣ የታላሚዋ ቁራጭ ልብስ ወ.ዘ.ተ. ተተኪዎቹ የፍትወት ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ (1905፣ ገጽ 153)፡፡

[11] ላካናውያን ***Metaphor*** የሚሉት ሲሆን የልቡና አሰራሮችን ከቋንቋ ጋር አዛምደው በመመርመር ከፍሮይዳውያኑ “እመቃ” (condensation) ጋር አቻ አድርገው ተጠቅመውበታል፡፡ “ልጅነት” በቋንቋ አማካኝነት የሚበለፅግ ማንነት ሲሆን እጅግ የፀነኑና ኢ-ግብረ ገባዊና ኢ-ማኅበራዊ ፍላጎቶች፣ ማንነቶችና በጥቅሉ ሰርካዊውን ህይወት የ“ሚንቁ” የኢ-ንቁ ልቡና እስቦች ደግሞ ከቋንቋ አቅም በላይና በሰርካዊው የልሳን ተራክቦ ህያው የሚሆኑ ባለመሆናቸው በ“እመቃ” እና የ“ቅጅዎች ፍለሳ” (displacement) በሰርካዊው ህይወት ውስጥ ኅልዮታቸውን ያገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ በ“metaphor” እና “metonomy” የቋንቋ አጠቃቀሞች የሚሆን ነው፡፡ ላካን፣ ***metaphor***ን ከ“እመቃ”፣ ***metonomy***ን ደግሞ ከ“ቅጅዎች ፍለሳ” ጋር አጎዳኝቶ የኢ-ንቁ ደመ-ነፍሳዊ ፍላጎቶች ከሰርካዊው ሥነ ልሳናዊ የትዕምርት ሒደት ጋር እየለዘቡ የሚከሰቱባቸው ናቸው ብሎ እንደሞገተ ምሁራን ይናገራሉ (ምሳሌ፡- Thom፣ 2003፣ ገጽ 36፤ Grosz፣1998፣ ገጽ 98-101)፡፡

Mijolla-Mellor, S. (2005). Spliting of the Ego. In Alain Mijolla (ed.), *International Dictionary of Psychoanalysis.* Trans. Philip Beitchman, *et al*. Vol. 1 (pp. 1647). New York: Thomson Gale.

Ribas, D. (2005). Sadism. In Alain Mijolla (ed.), *International Dictionary of Psychoanalysis*. Trans. Philip Beitchman, et al. Vol. 1 (pp. 1515-1526). New York: Thomson Gale.

Roussillon, R. (2005). Reality Principle. In Alain Mijolla (ed.), International Dictionary of Pschoanalysis. Trans. Philip Beitchman, et al. Vol. 1 (pp. 1450) New York: Thomson Gale.

Smada, C. (2005). Fixation. In Alain Mijolla (ed.), *International Dictionary of Psychoanalysis.* Trans. Philip Beitchman, *et al*. Vol. 1 (pp. 588). New York: Thomson Gale.

Sullivan, S (2004). The Unconscious Life of Race: Freudian Resource for Critical Race Theory. In John Mills (ed.), *Reading Freud: Psychoanalysis through Philolososphy* (pp.195-218). New York: SUNP,

Thom, M. (2003). The Unconscious Structured as a Language. In Slavoj Zizek (ed.), *Jacques Lacan: Critical Evaluations in Cultural Theory*. Vol. 1 (pp. 33-70) London and NewYork: Routledge.

Tyson, L. (2006). *Critical Theory Today: a User-Friendly Guide.* 2nd ed. NewYork & London: Routledge.

Wellek, R. and Warren, A. (1949). *Theory of Literature.* New York: Harcourt, Brace And Company Inc.

Zakin, E. (2004). The 'Alchemy of Identification': Narcism, Melancholia, Feminity. In John Mills (ed.), *Reading Freud: Psychoanalysis through Philosophy* (pp. 77-102). New York: SUNP.